በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

## ክፍል ሦስት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

የካቲት ፳፫ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

- እስካሁን ድረስ ባጠናነው የክርስትና ታሪክ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ኅልውናዋ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ የነበረና ትውፊቱና ትምህርቱም ሳይናወጽ የሕይወት መሥዋዕትነትም በመክፈል ተጠብቆ የኖረ መሆኑን በትክክል ተረድተናል ተቀብለናልም፡፡ ለዚያ ዘምን ከዚህችው አንዲት፤ ቅድስት፤ ሐዋርያዊትና ዓለም አቀፋዊት ቤ/ክ በቀር ለእውነት ምስክር - ጠበቃ የሆነ ሌላ ምንም ማንምም አልነበረም፡፡

- ቤተክርስቲያን ጌታችን በምሳሌ ባስተማረው ትምህርት እንደገለጸው በመጀመሪያ እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ፍሬ የነበረች ስትሆን እንደ ብርቱ ዛፍ ከፍ ብላ አድጋ ቅርንጫፎችዋን በዓለም ሁሉ አስፍታለች፡፡

- በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን፡ በቅድስት አገር ኢየሩሳሌም፤ ሶርያ፤ አርመን፤ ታናሽ እስያ፤ መቄዶንያ፤ ሮም፤ ግብጽ ... ቤተ ክርስቲያን (የክርስቲያኖች አንድነት - ማኅበር) ነበር፡፡ ይህችም በተክርስቲያን በጳጳሳት ትመራ ነበር፡፡ አብያተ ክርስቲያናትም በየአገሩ ሲስፋፉ በየአገሩ ማዕከል ፓትርያርኮች ተደረጉ፡፡

- የነበሩትም አብያተ ክርስቲያናት እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ በአምስት መንበር ይመሩ ነበር፡፡ እነሱም፡- የእስክንድርያ፤ የቁስጥንጥንያ፤ የአንጾኪያ፤ የኢየሩሳሌም እና የሮም ነበሩ፡፡ በመካከልም እንግዳ ትምህርት የሚያስተምሩ መናፍቃንን እያወገዙ በየዘመኑም የሚነሱ ፈተናዎችን ሁሉ በመቋቋም የአንዲቱ የክርስቲያኖች ቤ/ክ ጉዞ እስከ 451ዓ.ም. ድረስ ቀጥሏል፡፡

## ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን...

- ቤተክርስቲያንን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብሎ መሰየም የተወሰነው ከ4ኛ እስከ 5ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ተከስተው በነበሩ ሃይማኖታዊ ክርክሮች የተነሳ እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ከአርዮስ፤ መቅዶንዮስ፤ ንስጥሮስና #ክርስቲያን; ነን ከሚሉ ሌሎችም መናፍቃን የክህደት ትምህርት መለየት በማስፈለጉ ነው።

- ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል ከግሪክ የተወሰደ ሲሆን #ኦርቶ; እና #ዶኮስ; የሚሉ ሁለት ቃላትን የያዘ ነው። ትርጉሙም የቀና ቀጥ ያለ ምንጩ ከጌታችንና ከሐዋርያት የተገኘ ማለት ነው። ተዋሕዶ የሚለው ቃል ምንጩ ግዕዝ ሲሆን ያለመቀላቀል ያለመጣፋት አምላክ በተዋሕዶ ሰው ሰውም አምላክ ሆኗል ማለት ሲሆን ይኸም አባቶቻችን ንስጥሮስን ያወገዙበት ትምህርት ነው። ሃይማኖታችንን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብሎ የመጥራት ስያሜ ውሳኔዎች ምንጫቸው በ325፤ በ381 እና በ431 ዓ.ም. አባቶቻችን መናፍቃኑን በማውገዝ እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ያቆዩበት ጉባኤያት (የኒቂያ፤ የቁስጥንጥንያና የኤፌሶን) ናቸው።

- እነዚህም ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በየአገሩ አብያተ ክርስቲያናትን በማስፋፋት ፓትርያርኮች በበላይ ሆነው በሲኖዶስ ይመራሉ። ሲኖዶስም ሃይማኖታዊም ሆነ ቀኖናዊ ጉዳዮች ወይም ጥያቄዎች አስመልክቶ በየጊዜው በመሰብሰብ ውሳኔ ያስተላልፋል። አብያተ ክርስቲያናቱም ለተወሰነው ውሳኔ በመገዛት ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን ሲጠብቁ ኖረዋል።

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን…

- በአጠቃላይ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ በማይለይ በማይከፈል በእግዚአብሔር የባሕርይ፤ የመለኮትና የአገዛዝ አንድነት እንዲሁም በስም ሦስት አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ፡ በግብር አብ ወላዲ፤ ወልድ ተወላዲ መንፈስቅዱስን ከአብ የወጣ - ሠራፂ፤ በአካልም ለእያንዳንዳቸው ፍጹም አካል ፍጹም መልክ አላቸው ብለን እናምናለን፡፡ ማቴ 3፡16-17፤ ማቴ 28፡19-20፤ ዮሐ 15፡26፡፡

- እግዚአብሔር ዘላለማዊ፤ ጻድቅና በጽድቅም የሚፈርድ፤ዓለምን የፈጠረ ፈጥሮም የሚገዛ መሆኑን እናምናለን፡፡ ያለርሱም ፈቃድ በዚህ ዓለም የሚሆን አንዳች ነገርም የለም፡፡

- አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን በበደሉ ጊዜ ጨርሰው ይጥፉ ሳይል ሰውን ለማዳን ያለውን ዕቅድ መሲሁም ኢየሱስ የሚመጣ መሆኑን በነቢያቱ በኩል ተናግሯል፡፡ ጊዜውም ሲደርስ ኃጢአተኞችን ሊያድን እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም መጣ፡፡ እርሱም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በሃይማኖትና በጽድቅ እንዴት መኖር እንዳለብን አስተማረን፡፡

- በከበረ ደሙ ፈሳሽነትም በመስቀል ተሰቀሎ ኃጢአታችንን ሁሉ አጠበልን፡፡ ወደ መቃብርም ወርዶ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ በመነሳት በዘላለማዊት ርስት ለመኖራችን በኩር ሆነን፡፡ በሃምሳኛውም ቀን ዛሬም በቤተክርስቲያን የሚገኘውን ወደ እውነትና ጽድቅ የሚመራውን መንፈስቅዱስን ለሐዋርያት ላከ፡፡

## ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን...

- እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በዓለም ሁሉ በሚኖረው ክፉት በማትሸነፍና በማትወድቅ በአንዲት ቤተክርስቲያን እናምናለን፡፡ ቤተክርስቲያኒቱም ዓለም ዓቀፋዊት ናት፡፡ ማቴ 16:18

- በመንፈስቅዱስ በሚታደል የቤተክርስቲያን ጸጋ በጥምቀት፤ ሜሮን፤ ክህነት፤ ቊርባን፤ ንስሐ፤ ተክሊልና ቀንዲል እናምናለን፡፡ ጌታችንም ዳግመኛ ይህን ዓለም ለማሳለፍ እንደሚመጣ ሁሉም እንደ ሥራውም የሚቀበልበትም የፍርድ ቀን እንዳለ ጻድቃን መንግሥተ ሰማያትን ሲወርሱ ኃጥአን ወደ ገሃነመ እሳት እንደሚጣሉ እናምናለን፡፡

- ለመዳን እምነት ብቻ ሳይሆን እንደ ሃይማኖቱ ትምህርት መኖር ወይም ሥራ አስፈላጊ እንደሆነ፤ በዚህም የተነሳ አሥርቱን ትእዛዛትና በወንጌል የታዘዝነውን ሁሉ መፈጸም እንደሚገባ እናምናለን፡፡ በወንጌል ጌታ ያዘዘን አንዱ ትምህርት ... ጠላትን መውደድ ነው፡፡ ማቴ 5:43-45፡፡

- በክርስትና ያለው የፍቅር ሕግ ቤተክርስቲያንን በዓለም መካከል የምትፈለግ የሰላም መንገድ ያደርጋታል፡፡ ባልንገራችንን ካልወደድን፤ ይቅርም የማንባባል ከሆነ ጦርነትና ውድመት የማይቀሩ ናቸው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን...

- ጌታችን አባታችን ሆይ ስለሚለው ጸሎት ባስተማረበት ክፍል የበደሉንን ይቅር ስለማለት እንዲሁም በሌላ ክፍል ደግሞ በተሰጠን ስጦታ ማትረፍ እንደሚገባን አስተምሮናል፡፡ እውነተኛ እምነት በውስጥ በሚኖረው እድገት ዘወትር የበጎ ምግባራት ባለቤት መሆን ይገባዋል፡፡ #ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነውና፡፡; ያዕቆብ 2፡6፡፡

- ክርስቲያኖች ቁሳዊነት የማይገዛቸው ባላቸው ሁሉ የሌላቸውን የሚራዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ኩራት፤ ትዕቢት፤ ራስን መውደድ... በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው፡፡

- ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ሰው በእግዚአብሔር በነጻ ፈቃድ የተፈጠረ መሆኑንና ለእያንዳንዱ ሥራውም ተጠያቂ እንደሆነ ታስተምራለች፡፡

- እግዚአብሔር የሚወደንና ኃጢአተኞችንም ይቅር የሚል ነው፡፡ በማንኛውም ሁናቴ ይልቁንም ስንጠራው የሚረዳን አምላክ ነው፡፡ #ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል፡፡; በማለት ቃል ገብቶልናልና፡፡ ማቴ 7፡7

- በጎ ያልሆነ ነገር ሲገጥመን ወይም ስንታመም እግዚአብሔርን መውቀስ ሳይኖር ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥቅምና ከኃጢአታችንም ሊያነጻንና ለበጎ ነገርም የበቃን ሊያደርገን የመጣ እንደሆነ ተረድተን #ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን ብለን ; መጸለይ ይኖርብናል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን…

- ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ቅዱሳንን ታከብራለች፡፡ የእመቤታችንን፤ ነቢያትን፤ ሐዋርያትን፤ ሰማዕታትን፤ ጻድቃንን፤ ቅዱሳን አንስትን የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ወዳጆች ናቸው ብላ ታስተምራለች ታምናለች፡፡ ኢሳ 56 ፡ 1 - 12

- ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩም የጠበቀ ግኑኙነታችን አይበጠስም፡፡ እነርሱ ወደ ሰማያዊቱ ቤተክርስቲያን ይሻገራሉ፡፡ ራእይ 11 ፡ 19 በእግዚአብሔርም ዙፋን ፊት ወደ እግዚአብሔር ርስት እንድንደርስ ስለ እኛ ያማልዳሉ፡፡

- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክ አምልኮት ለምዕተ ዓመታት በተገነባው እና በአባቶቻችን ሐዋርያት፤ አበው ሐዋርያትና ቅዱሳን በተሰራው ሥርዓት መሠረት ይፈጸማል፡፡ ዋናው የአምልኮት ሥርዓት የሚፈጸመው በሥርዓተ ቅዳሴ ነው፡፡ የቅዳሴውም ማዕከሉ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙም መቀበል ነው፡፡ ዮሐ 6፡54

- ማንኛውም አማኒ ወደ ቅዱስ ቁርባን ከመቅረቡ በፊት ንስሐ መግባት ኃጢአቱን መናዘዝ ይጠበቅበታል፡፡ #አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር፡፡; የሐ. ሥራ 19፡18፡፡ እንዲሁም 1ኛ ቆሮ 11 ፡ 27-31፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን...

- ለሥጋ ፈቃድ፤ ለኃጢአት ያለንን ፍላጎት ለማሸነፍ ይረዳን ዘንድ ጾም በቤተክርስቲያን መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። በቤተክርስቲያንም ሰባት አጽዋማት ይገኛሉ። እነሱም ጾመ ነቢያት፤ ገሃድ፤ ነነዌ፤ ሁዳዴ፤ ድኅነት፤ ሐዋርያትና ፍልሰታ ናቸው።ሉቃስ 2፡37።

- ጌታችን ስለ ኃጢአት በራስ መፍረድ እንደሚገባም አስተምሮናል። #እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።; ማቴ 7፡1።

- በመጨረሻም #እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።; እንዳለ ቤ/ክ የፍጹምነትን መንገድ የምትከተልና የምታስተምር ልጆችዋም ወደ ፍጹምነት ጉዞ የሚያደርጉ ናቸው። ማቴ 5፡48። #በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁምል ያበረታችሁማል።; 1ኛ ጴጥ 5፡10።

- እንግዲህ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትዋና ትምህርትዋ ከብዙው እጅግ በጥቂቱ ይኸንን ይመስላል።

ይቀጥላል

… ሌሎችስ?

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።